# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

# *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም
April 24, 2015

## አይሲስ እየተባለ የሚጠራው ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረገውን አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በጥብቅ ያወግዛል!

በአገራችን የተንሰራፋው ኢ-ሰብዓዊ አምባገነን መንግሥት በብዙሃኑ ሕዝብ ላይ በሚያደርሰው የኤኮኖሚ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እንዲሁም ሃይማኖታዊ በደሎች ምክንያት ሕዝባችን በሰላም ለመኖር ባለመቻሉ አገር ጥሎ እየተሰደደ ነው። ከድጡ ወደማጡ እንዲሉ በተሰደደበት አገርም ቢሆን የሕይወት ዋጋ በመክፈል ላይ መሆኑ እጅግ አሳዛኝ ነው።

አምና በሳውዲ ዓረቢያ በግፍ የተገደሉና የተደበደቡ በየእሥር ቤቱ ተወርውረው የት እንዳሉ እንኳን የማይታወቁ ወገኖቻችን ቁጭት ገና ከአዕምሯችን ሳይወጣ፣ ዘንድሮ ደግሞ በየመን ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከፍተኛ ስጋት ላይ በመውደቃቸው ጭንቀታችን ከፍ ብሏል። እስካሁንም ድረስ የመከራ ደመና በላያቸው ላይ እንዳንዣበበ ለመሆኑ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። ሌሎች አገሮች ዜጎቻቸውን ከየመን ሲያስወጡ የኢትዮጵያ አምባገነን መንግሥት ግን የማስወጣው ፓስፖርት ያላቸውን ብቻ እንጂ፣ ፓስፖርት የሌላቸው ኢትዮጵያዊ ቢሆኑም አናወጣቸውም ብሎ ከእሣት ውስጥ ትቷቸዋል። ፓስፖርት ያለው የመንግሥት ወኪልና ሀብታም ነጋዴ እንጂ በደል ደርሶበት ከአገሩ የተሰደደ ዜጋ ሊኖረው እንደማይችል ለማንም ግልጽ ነው። ለመሆኑ ኢትዮጵያዊነት በፓስፖርት መለካት አለበትን?

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች በከፍተኛ የሃዘንና የቁጭት ድባብ ውስጥ ጥለውን እያለ፣ አሁን በቅርቡ ደግሞ በደቡብ አፍሪቃ ውስጥ በውጭ ሀገር ዜጎች ላይ ያነጣጠረው ጥላቻ እጅግ ዘግናኝና ኢ-ሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ ኢትዮጵያውያንን በአደባባይ በእሳት ሲያጋዩአቸው እያየን ነው። ይህ ድርጊት ወገኖቻቸውን ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን፣ የዓለምን ሕዝብ ጭምር አንገሽግሾ ሰቀቀን ውስጥ የጣለ ሰብዓዊነት የጎደለው አረመኔያዊ ድርጊት ነው። የደቡብ አፍሪቃው መዓት ሳይበርድ እነሆ አሁን ደግሞ ሌላ ችግር ተከሰተ። የአሁኑስ ይባስ ብሎ ጥቃትን ተላብሶ፣ ጥቃት ጥቃት እየገለማ አንቀጠቀጠን፣ አንገፈገፈን፣ የምንይዘው የምንጨብጠውን አሳጣን። ጥቃት ከጥንብ ይገማልና።

ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ በአገራችው መኖር ያልቻሉ ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በስደት አገር ነፃነታችን ይከበራል፣ ሠርተን እራሳችንንና ደሃ ወላጆቻችንን እንረዳለን ብለው በተሰደዱበት በሊቢያ ውስጥ፣ አይሲስ በተባለ አክራሪ እስላማዊ ቡድን 30 ኢትዮጵያውያንን በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ውስጥ ገሚሶቹን አንገታቸውን በሰይፍ ሲቀላ፣ ገሚሶቹን ደግሞ በጥይት ደበደባቸው። ይህ

P.O.Box 8141
Silver Spring, MD 20910

P.O.Box 88675
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078

Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

እጅግ አሰቃቂ አገዳደል ሃዘናችንንና ቁጭታችንን አባብሶታል። በአገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያንን ከፍተኛ የሃዘን ጨለማ ውስጥ ጥሎናል።

እንዲሁም አዲስ አባባ ያሉ የሟች ቤተሰቦችና ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን መስቀል አደባባይ ወጥተን ሃዘናችንን በልቅሶ እንግለጽ ብለው በእንባ እየተራጩ በነበሩበት ወቅት የአገዛዙ ወታደሮች ከሳውዲ አረቢያውና ከደቡብ አፍሪቃው ባልተናነሰ ሁኔታ ወገኖቻችን በፖሊስ ቆመጥ ሲቀጠቀጡ ውለዋል። ብዙዎችም ወደ እሥር ቤት እንደተወሰዱ የዜና አውታሮች ዘግበዋል።

ጨካኙ አይሲስ እየተባለ የሚጠራው ቡድን የእስልምናን ሃይማኖት የሚወክል ሳይሆን፣ ሰይጣናዊ ተልዕኮ ያለው አክራሪ ቡድን ለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል። እስከምናወቀው ድረስ በአገራችንና በባህላችን የእስልምና እምነት ተከታዮች ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጋር ክፉና ደጉን ተካፍለው በአንድነት ሲኖሩ እንጂ እንደዚህ ያለ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ሲፈጽሙ አይተንም ሰምተንም አናውቅም።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ይህን ቁልጭ ያለን ሃቅ ላለመቀበል የኢትዮጵያ መንግሥት ተብዬው ኢትዮጵያውያን ለመሆናቸው መረጃ አላገኘንምና እርምጃ ለመውሰድ እንቸገራለን ሲል መደመጡ የሕዝባችንን ሃዘን እጥፍ ድርብ እንዲሆን አድርጎታል። ልባችንንም አቁስሎታል። አሁንም የሃዘን ቀን እናክብር ብሎ የተነሳው ሕዝቡ ከቁጥጥሩ ውጭ እየሆነ በመምጣቱ መተንፈሻ መንገድ ፈልጎ እንጂ ለሟቾች ግድ እንደሌለው እስካሁን በደረሱ በደሎች ከወሰዳቸው እርምጃዎች መረዳት ይቻላል።

ውድ ኢትዮጵያውያን! በሀገራችን የዴሞክራሲ መብት ተግባራዊ እንዲሆን፣ ሰው በችሎታው ሠርቶ የሚኖርባት አገር እንድትሆን፣ ወገኖቻችን በሀገራቸው ኮርተው ከስደትና ከመከራ እንዲድኑ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት የሚደረገውን ትግል ማጠናከር ይኖርብናል፤ ይጠበቅብናልም። ይህን እውን ለማድረግም በአንድነት መቆም የግድ ነው። በየቀኑ ሃዘን ላይ እየቆምን ማልቀስ አይጠቅምም። አንድነት ኃይል ነውና በአንድነት እንቁም። የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነታችንን አቻችለን በመተባበር ይህን በአገራችን እንዳንኖር የሚያደርገውን ሥርዓት ለማስወገድ ጠንክረን መታገል ይኖርብናል። ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ለጋራ ችግራችን የጋራ መፍትሄ ለመሻት በአንድነት ሆነን እንታገል በማለት በተደጋጋሚ ጥሪውን አቅርቧል፤ አሁንም ያቀርባል። በጋራ ታግለን ይህንን ለዜጎቹ ደንታ የሌለውን አገዛዝ ማስወገድ ካልቻልን የአገር ሕልውናችንን አጥተን የዓለም ሕዝብ መዘባበቻ ሆነን እንዳንቀር እንሰጋለን።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በወገኖቻችን ላይ በተፈጸመው ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ጥልቅ ሃዘን የተሰማው መሆኑን እየገለጸ፣ ለሟች ቤተሰቦች መጽናናቱን እንዲሰጥልን እንመኛለን፤ የሞቱትንም ነብስ ይማር።

ለወገኖቻችን መብቶች መከበር በጋራ እንታገል!